810 00 230/53
17/06/2009

744/2013

ለከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ

ከ/ል/ቤ/ሚ/ር

ጉዳዩ፡-የጸደቀ መመሪያ ስለመላክ

7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የፋይናንስና ሎጂስቲክ አቅርቦት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 56/2009 ሆኖ ከጥር ወር 2009 ዓ.ም ጀምሮ በሚኒ ካቢኔ የጸደቀ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በዚሁ መሠረት የመመሪያውን ተፈጻሚነት እንድትከታተሉና እንድታስፈጸሙ የጸደቀ 1 ጥራዝ መመሪያ /ሰነድ/ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጎ የተላከ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

አምባቸው መኮንን ሲሳይ (ዶ/ር)
ሚኒስትር

ግልባጭ

- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ /የከተማ ልማት ዘርፍ /
- ለክቡር ሚኒስተር ዴኤታ/የቤቶች ዘርፍ /
- ለሚኒስተር ጽ/ቤትና ሚኒ ካቢኔ ጉዳዮች ቢሮ
- ለሕግ ዳይሬክቶሬት

ከ/ል/ቤ/ሚ/ር

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT AND HOUSING

የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም
ETHIOPIAN URBAN FORUM

7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም
የፋይናንስና ሎጂስቲክ አቅርቦት አፈፃፀም መመሪያ
ቁ. 744/2013

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር * The Federal Democratic Republic of Ethiopia * Ministry of Urban Development & Housing

ጥር 2009 ዓ.ም

ማውጫ

ገፅ

መግቢያ 3

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ 4
2. ትርጓሜ 4
3. የመመሪያው ዓላማ 5
4. የፋይናንስ መመሪያ መርሆዎች 5
5. የግዢ መመሪያ መርሆዎች። 5

ክፍል ሁለት

የፎረሙ የፋይናንስ አሰራሮች

6. የባንክ ሂሳብ አሰራር 6
7. የቼክ ፈራሚዎች አደረጃጀት። 6
8. የቼክ ጥራዞች አያያዝና የክፍያ አፈጻጸም። 6
9. የገቢ መዋጮ ሂሳብ አያያዝ½ 7
10. ክፍያን በተመለከተ አጠቃላይ የአፈፃፀም ሁኔታ½ 8
11. የገቢና የክፍያ ሰነዶች አጠቃቀም። 8
12. ጎንደር ከተማ የሚተላለፈውን የሥራ ማስኪያ ሂሣብ በተመለከተ። 8
13. የውሎ አበልና ልዩ ልዩ ክፍያዎች። 9

ክፍል ሦስት

የፎረሙ የግዥ አሰራሮች

14. የተመረጡ የግዥ ዘዴዎች። 10
15. የግዥ አፈጻጸም ሂደት። 10
16. የመመዝገቢያ ክፍያ። 12
17. የኤግዚብሽን ቦታ /ድንኳን/ ኪራይ አከፋፈል። 12
18. ከስፖንሰሮች የሚገኝ ገቢን በተመለከተ። 13
19. የገቢና ወጪ በጀት ግምት። 13

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ አሰራሮች

20. የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት። 14
21. የቢሮ ዝግጅት። 14
22. ሂሣብ ማስመርመር። 15
23. መመርያውን ስለ ማሻሻል 15
24. መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ። 15

መግቢያ

በኢትዮጵያ ፈጣን የከተሞች መስፋፋትን ተከትሎ የከተማ ነዋሪዎችንና የሌሎች ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ በማጠናከር መልካም ተሞክሮዎችንና ልምዶችን በማስፋፋት የከተማ ልማት ፖሊሲውን፣ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን ትግበራና ስኬት ማፋጠን ይቻል ዘንድ አመታዊ የከተሞች ሳምንት የተሰየመ ሲሆን፣ በዚሁም መነሻነት ቀደም ሲል አንደኛው፣ ሁለተኛው፣ ሶስተኛው፣ አራተኛው እና አምስተኛው የከተሞች ሳምንት እንዲሁም ስድስተኛው የከተሞች ፎረም በተለያዩ ከተሞች የተካሄደ ሲሆን በተመሳሳይ መልኩ 7ኛዉ የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በጎንደር ከተማ ከሚያዝያ 22- 28 ቀን 2009 ዓ.ም የሚከበር በመሆኑ፣

እንደሚታወቀው ማንኛውም ተቋም የተሰጠውን ተግባርና የተጣለበትን ኃላፊነት በሚገባ ሊያከናውን የሚችለው የተጠናከረ የገቢ ምንጭና በትክክል የተደራጀ የፋይናንስና አቅርቦት አመራር ስልት ሲኖረው መሆኑ አጠያያቂ አይደለም። የተደራጀና የተጠናከረ የፋይናንስና አቅርቦት አመራር ሲባል አንድ ተቋም የሚሰበስበውን ገቢ፣ የሚያወጣውን ወጪና አቅርቦት እንዴት በተግባር ላይ እንደሚያውለው የሚከተለው የአሠራር ስልት ማለት ነው። ለዚህም የፋይናንስ ዕቅድና የፋይናንስ አያያዝ መመሪያዎችን እንዲሁም የአቅርቦት አፈጻፀም መመሪያ ማዘጋጀትና ሥራ ላይ ስለሚውልበት ሁኔታ አመቺ ስልት መቀየስ፣ የተሟላና ተገቢ የሆነ የሒሳብና የአቅርቦት መዝገብ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

ስለሆነም 7ኛውን የኢትዮጵያ የከተሞች ፎረም ዝግጅት በአግባቡ ለማካሄድ የሚሰበሰበውን ገንዘብ በኃላፊነት እንዲመራ የተደራጀ ኮሚቴና የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ሥራቸውን ሲያከናውኑ የሚፈለግባቸውን ተግባር ጠንቅቀው ሊያውቁ ይገባል። ከዚህ አኳያ የሚያከናውኑትን የዕለት ተዕለት ሥራ በአግባቡ ለማከናወን የሚረዳ የፋይናንስና ሎጂስቲክ የአቅርቦት አፈፃፀም መመሪያ ሊኖር የሚገባ በመሆኑ ይህ አጭር የፋይናንስና ሎጂስቲክ የአቅርቦት አሠራር መመሪያ ተዘጋጅቷል።

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Urban Development & Housing

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የ7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የፋይናንስና የሎጂስቲክ አቅርቦት አፈፃፀም መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) ገቢ/መዋጮ" ማለት ለ7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ዝግጅት ማከናወኛ ከመመዝገቢያ፣ ከድንኳን ኪራይ፣ ከስፖንሰሮች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚሰበሰብ ነው፡፡
2) "ወጪ" ማለት ከ7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ሥራ ጋር በተገናኘ በተገቢው አካል ሲፈቀድ የሚፈፀም ክፍያ ነው፡፡
3) "ከተማ አስተዳደር" ማለት 7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ላይ የሚሳተፉ ከተሞች ናቸው፡፡
4) "አቅርቦት" ማለት ለ7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በዓል አከባበር የሚውል ማንኛውም አይነት በግዥ፣ በስጦታ እና በትውስት የሚቀርብ ቁሳቁስ እና አገልግሎት አቅርቦት ነው፡፡
5) "የከተሞች ፎረም" ማለት በተመረጡ ከተሞች በዙር የሚከበረው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በዓል ነው፡፡
6) "ኮሚቴ" ማለት በ2009 ዓ.ም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በጎንደር ከተማ አስተዳደር ለሚከበረው የ7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረምን አስመልክቶ የተለያዩ ስራዎችን እንዲያከናውኑ የተቋቋሙ የአብይ ኮሚቴ፣ የቴክኒክ ኮሚቴ እና ንዑሳን ኮሚቴዎች ናቸው፡፡
7) "ሎጂስቲክ" ማለት ለ7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም አገልግሎት የሚውል የዕቃ እና የአገልግሎት አቅርቦት ነው፡፡
8) "ስፖንሰርሽፕ" ማለት ለ7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በዓል አከባበር በገንዘብ ወይም በአይነት ድጋፍ የሚያደርጉ ማለት ነው፡፡
9) "የውሎ አበልና ልዩ ልዩ ክፍያዎች" ማለት ለ7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በዓል ተሳታፊዎች የሚከፈል የቀን አበል ማለት ነው፡፡
10) "ልዩ ልዩ ክፍያዎች" ማለት ከ7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በዓል አከባበር ጋር በተያያዘ ለዕቃ ግዥና ለአገልግሎት የሚከፈሉ ማንኛውም ወጪ ማለት ነው፡፡

3. የመመሪያው ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ የ7ኛውን የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን እንዲቻል የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለመሰብሰብ፣ ግዥ ለመፈፀም፣ በአግባቡ ክፍያ ለመፈፀም፣ ተገቢውን ምዝገባ በማካሄድ ሂሣቡን ለማስመርመር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት ነው።

4. የፋይናንስ መመሪያ መርሆዎች

የከተሞች ፎረም ፋይናንስን ከማንቀሳቀስ አኳያ የሚከተሉትን የፋይናንስ አሠራር መርሆዎችን መከተል ይገባል።

1) 7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም አከባበር ጋር በተያያዘ የሚገኙትን ሂሳቦች ተቀባይነት ባላቸው የፋይናንስ አሠራር መርሆዎች መሰረት ማከናወን፣

2) በመንግሥት የፋይናንስ መመሪያዎች መሠረት ከፎረሙ አከባበር ጋር በተያያዘ ያለውን ሂሣብ መዝግቦ በአግባቡ መያዝ፣

3) ከፎረሙ አከባበር ጋር የተያያዙ ገቢዎችን መሰብሰብ እና በጥንቃቄ እንዲያዝ ማድረግና ወጪዎችን መክፈል፣

4) ለሦስተኛ ወገን ተጠቃሚዎች የሚውሉ መደበኛና ልዩ የሒሳብ መግለጫ ሪፖርቶችን ማዘጋጀትና ማስመርመር ከፋይናንስ አንፃር የሚከናወኑ አበይት ተግባራት ናቸው።

5. የግዢ መመሪያ መርሆዎች፣

1) 7ኛውን የከተሞች ፎረም ለማሳካት የሚያስፈልጉ የአገልግሎት እና የዕቃ ግዥዎችን በተሟላ መልኩ በማቅረብ ሂደት በግዥ አፈጻጸም ቁጠባን መሰረት ያደረገ መሆን ይገባዋል።

2) የአፈጻም ብቃትን እና ውጤታማነትን በሚያረጋግጥ፣ የሚፈለገው የአገልግሎትና የዕቃ ዓይነት ደረጃውን የጠበቀና ፍላጎትን በሚያረካ መልኩ በአጭር ጊዜ ውስጥ በማሟላት ፕሮግራሙን ማሳካት ይኖርበታል።

3) የሚከናወነው የግዥ ሂደት የመንግስትን የግዥ እና የፋይናንስ ደንብና መመሪያ የተከተለ መሂን አለበት፣

4) ፕሮግራሙን በማስፈጸም ረገድ በተቋቋመው አብይ ወይም የቴክኒክ ኮሚቴ ግዥው ሲፈቀድና ሲጸድቅ የሚከናወን ይሆናል።

5) የሚገዙ የቋሚ ዕቃዎች በጥንቃቄ እንዲያዙና በቀጣይነት ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና ለቀጣይ ዙር የከተሞች ፎረም በዓላት አከባበር አገልግሎት ላይ እንዲውል ለማድረግ በአግባቡ ተመዝግበው እንዲያዙ ይደረጋል።

ክፍል ሁለት

የፍረሙ የፋይናንስ አሰራሮች

6. የባንክ ሂሳብ አሰራር

1) የከተሞች ፎረምን ለማካሄድ ከተለያዩ አካላት የሚሰበሰበውን ገንዘብ ከዚህ በታች በተመለከተው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በሚገለገልበት የባንክ ሒሳብ ቁጥር ገቢ አድርጎ ሥራ ላይ ማዋል፡፡

2) ፎረሙ የሚጠቀምበት የባንክ ሂሳብ ቁጥር "በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ስም ለፎረሙ አገልግሎት በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ቁጥር" ይሆናል፡፡

3) ለ7ኛው ከተሞች ፎረም የሚሰበሰበውን እና ወጪ የሚደረገውን የሂሳብ እንቅስቃሴ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በከተሞች ገቢ ማሻሻል፣ ፈንድ ሞብላይዜሽን እና ፋይናንስ ቢሮ ስር የሚገኘው የገንዘብ ማሰባሰብ፣ ክፍያና ሂሳብ ምዝገባ ዳይሬክቶሬት ሃላፊነት ሥር የሚንቀሳቀስ ይሆናል፡፡

4) በዚህ የባንክ ሒሳብ ቁጥር ከጥር 1 ቀን 2009 ዓ.ም. ጀምሮ ከተለያዩ አካላት ለከተሞች ፎረም ዝግጅት ገቢ የተደረገው ገንዘብ ለእዚሁ ዓላማ ይውሳል፡፡

5) የባንክ ሂሣቡን ለማንቀሳቀስ የሚረዱ የቼክ ጥራዞችን የባንክ ሂሣብ አንቀሳቃሽ በሆኑ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የጋራ ፈራሚዎች ለባንኩ ጥያቄ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

6) በየወሩ የባንክ ሂሣብ እንቅስቃሴ መግለጫ ሪፖርት(Bank Statement) ሂሣቡ ከተከፈተበት ባንክ በማምጣት ሂሣቡ ከምዝገባው ጋር መታረቅ ይኖርበታል -(Bank Reconciliation)፡፡

7. የቼክ ፈራሚዎች አደረጃጀት፣

የቼክ ፈራሚዎች አደረጃጀት በበጀት አመቱ በስራ ላይ ባለው የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር አሰራር የፊርማ ውክልና መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

8. የቼክ ጥራዞች አያያዝና የክፍያ አፈጻጸም፣

1) የከተሞች ፎረምን ሂሳብ ለማንቀሳቀስ ከባንክ የተሰጡ የቼክ ጥራዞች በአግባቡ መቀመጥ ይገባቸዋል፡፡

2) ለእያንዳንዱ የቼክ ወጪ የክፍያ ማዘዣ መዘጋጀት አለበት፡፡

3) ቼኮች በሥራ ላይ የሚውሉት በተሰጣቸው የቁጥር ቅደም ተከተል መሠረት ብቻ መሆን አለበት፡፡

4) ጉርድ ቼኮችን የያዙ ጥራዞች (ያለቁ ቼኮች) የሂሣብ ምርመራ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በሚመደበው የፋይናንስ ባለሙያ እጅ ሊቀመጡ ይገባል::

5) ክፍያ የተፈፀመባቸው የቼክ ቁጥሮችን የያዙ የክፍያ ማዘዣዎች በሂሣብ መዝገብ /ዕብእሐ ላይ መመዝገብ ይኖርባቸዋል::

6) ክፍያ የተፈጸመባቸው ተጎራጅ ቼኮች በኦዲተር ሲጠየቁ እንዲቀርቡ ይደረጋል::

9. የገቢ መዋጮ ሂሳብ አያያዝ፣

1) ቀደም ሲል በተጠቀሰው የባንክ ሂሣብ ውስጥ የግለሰብ ገንዘብ ገቢ ሊደረግ አይችልም::

2) የክፍያ ቀናቸው ያልደረሰ ወይንም ያለፉ ቼኮችን መቀበል አይፈቀድም::

3) የግለሰብ ቼኮችን መቀበል የሚቻለው ግለሰቡ በባንክ ሂሣቡ ውስጥ ገንዘብ ያለው መሆኑን ባንኩ ሲያረጋግጥ ብቻ ነው:: በሌላ በኩል በCPO መልክ ተዘጋጅቶ የቀረበን መዋጮ ገቢ ማድረግ ይቻላል::

4) በጥሬ ገንዘብ የተሰበሰቡ ገቢዎች በተቻለ መጠን በዕለቱ ባንክ መግባት ይኖርባቸዋል::

5) ገቢዎችም ሆኑ ወጪዎች በዕለቱ መመዝገብ አለባቸው::

6) የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኞች በአግባቡ መቀመጥ ይኖርባቸዋል::

7) የገንዘብ መቀበያ ደረሰኞች ተከታታይ ቁጥር ሊኖራቸው ይገባል::

8) ጥሬ ገንዘብ እንዲይዝ የተመደበው ሰው ገንዘቡን በአግባቡ ስለመቀበሉ፣ ስለማስቀመጡና ስለመክፈሉ ሙሉ በሙሉ ተጠያቂ ይሆናል::

9) ገንዘብ ሰብሳቢውና የሂሣብ መዝገብ የሚይዘው ሰው የተለያየ መሆን ይኖርበታል::

10) በየዕለቱ የሚሰበሰበው ገንዘብ ሳይቀነስ በዕለቱ ባንክ እንዲገባ መደረግ ይኖርበታል::

11) አስገዳጅ ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ከተሰበሰበ ገቢ ላይ ክፍያ መፈፀም አይቻልም::

12) በእጅ የሚያዘው ጥሬ ገንዘብ በተቻለ መጠን አነስተኛ ብር 70,000.00 /ሰባ ሺህ/ መሆን ይኖርበታል::

13) የሦስተኛ ወገን ወይንም የግል ገንዘብ ከዚህ ሂሣብ ጋር መቀላቀል አይኖርበትም:: ሆኖም የሚኒስቴር መቤቱ የሚያንቀሳቅሳቸው ፕሮጀክቶች ገንዘብ ገቢ ሲደረግ በተቀዕላ ሌጀር መለየት ይኖርበታል::

10. ክፍያን በተመለከተ አጠቃላይ የአፈፃፀም ሁኔታ፣

1) የክፍያው ምክንያት ምንም ዓይነት ቢሆን ለክፍያው መነሻ የሚሆኑ ደጋፊ ሰነዶች ቀርበውና በሚመለከተው ኃላፊ ታይተው ትዕዛዝ ሊሰጥባቸው ይገባል::

2) ማንኛውም ክፍያ እስከ ብር 50,000.00 /ሀምሳ ሺህ/ ድረስ በቴክኒክ ኮሚቴ ሰብሳቢ መፈቀድ ይኖርበታል:: ሆኖም የቴክኒክ ኮሚቴ ሰብሳቢ በሌሉበት በአብይ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይም በበላይ አመራሩ መፈቀድ ይኖርበታል::

3) ከብር 50 ሺህ በላይ ለሆኑ ክፍያዎች በአብይ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይም በበላይ አመራሩ መፈቀድ ይኖርበታል::

4) ከ50 ሺህ በላይ ለሆኑ ማንኛውም ወጪ በአብይ ወይም በቴክኒክ ኮሚቴ ቃለ-ጉባኤ የተደገፈ ሊሆን ይገባል::

5) የክፍያ ግዴታ ከመገባቱ በፊት በቂ የገንዘብ መጠን መኖሩ መረጋገጥ ይኖርበታል::

6) የክፍያዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚከተሉትን መመርመር ያስፈልጋል፣

ሀ) ክፍያው ተመጣጣኝና ለተገቢው ተግባር መሆኑን፣

ለ) ክፍያውን ያፀደቀው ሰው ውክልና የተሰጠው መሆኑን፣

ሐ) ለክፍያ የሚፈለጉት ሰነዶች በሙሉ የቀረቡና ሰነዶቹም ዋና ቅጂዎች መሆናቸውን፣

መ) የሂሣብ ስሌቱ ትክክል መሆኑን፣

ሠ) በሕግ የታወቁ ታክሶች መቀነሳቸውን ማረጋገጥ::

7) ክፍያዎችን በቼክ፣ በባንክ ሂሣብ በዝውውር፣ ወይንም ለጥቃቅን ወጪዎች ከተመደበው ገንዘብ ላይ በጥሬ ገንዘብ መፈፀም ይቻላል::

8) ክፍያዎች የሚፈፀሙት ስማቸው በክፍያ ማዘዣው ላይ ለተጠቀሱት ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ብቻ ነው::

11. የገቢና የክፍያ ሰነዶች አጠቃቀም፣

1) ሂሣብ አያያዝን በተመለከተ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሒሳብ መዝገብ አያያዝና የገንዘብ ያዥ የአሰራር ሥርዓትን የተከተለ ይሆናል::

2) ወጪዎችና ገቢዎችን ለመመዝገብም ሆነ ገንዘብ ለመቀበልና ክፍያን ለመፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች/የገቢና የወጪ ደረሰኞች፣የክፍያ ማዘዣ ቅጾች፣ ወዘተ/ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚጠቀምባቸው የፋይናንስ ሰነዶች ይሆናሉ::

12. ጎንደር ከተማ የሚተላለፈውን የሥራ ማስኬጃ ሂሣብ በተመለከተ፣

1) ከፎረሙ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ወጪዎችን ለመሸፈን ቀደም ሲል ከተጠቀሰው የባንክ ሂሣብ ቁጥር ካለው ሂሣብ ውስጥ የጎንደር ከተማ አስተዳደር በዕሁፍ በሚያሳውቀው የባንክ ሂሣብ ቁጥር የተፈቀደው ገንዘብ ይተላለፋል::

2) ለጎንደር ከተማ አስተዳደር ገንዘቡ ከመላኩ በፊት ዝርዝር ወጪዎቹ በቅድሚያ ቀርበው በአብይ ኮሚቴው መፅደቅ ይኖርባቸዋል::

3) በቅድሚያ ለጎንደር ከተማ አስተዳደር የተፈፀሙ ክፍያዎች በፌዴራል የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ወጪ ከተደረጉ በኂላ በሚቀርቡት ሕጋዊ የወጪ ማስረጃዎች መሠረት መወራረድ ይኖርባቸዋል:: ሆኖም በክልሉ የፋይናንስ እና ግዥ መመርያ መሰረት የተፈፀመ ከሆነ የክልሉን መመርያ በማሀተም በማረጋገጥ ከወጪ ሰነዱ ጋር መቅረብ ይኖርበታል::

13. የውሎ አበልና ልዩ ልዩ ክፍያዎች፣

1) የውሎ አበል ክፍያ አፈፃፀም በተመለከተ በዐብይ ወይም በቴክኒክ ኮሚቴው ፀድቆ በሚቀርበው ዝርዝርና የቀን ብዛት መሠረት ክፍያ ይፈፀማል::

2) ለአንድ የከተሞች ፎረም ተሳታፊ በቀን ብር 400.00 /አራት መቶ ብር/ የውሎ አበል ለሚቆይበት ቀን ተሰልቶ የማይወራረድ እና የማይቆራረጥ ሂሳብ የሚከፈል ይሆናል:: ሆኖም ጉዞውን ማጠናቀቁ እንዲታወቅ የማወራረጃ ፎርሙን ተጓዥ ሞልቶ እና በንዑስ ኮሚቴ ሰብሳቢ እና በቴክኒክ ኮሚቴ ሰብሳቢ አስፈርመው ማቅረብ ይኖርባቸዋል::

3) ፎረሙ ከሚካሄድበት ከተማ ለፓናል ውይይት ጥሪ ተደርጎላቸው ለሚሳተፉ በፓናል ንዑስ ኮሚቴ ዝርዝራቸው ቀርቦና በዓብይ ውየመ በቴክኒክ ኮሚቴው ሲፈቀድ ለእያንዳንዳቸው በቀን ብር 100.00 /አንድ መቶ ብር/ ሂሳብ ለተሳተፉበት ቀን ተሰልቶ የማይወራረድ ሂሳብ ይከፈላል::

4) በተራ ቁጥር ሦስት የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ በፓናል ን/ኮሚቴ የሚቀርበው ዝርዝር እና የሚከፈለው የገንዘብ መጠን በዓብይ ውየመ በቴክኒክ ኮሚቴ ሲፈቀድ ክፍያው በጎንደር ከተማ አስተዳደር በኩል ተፈፅሞ የተሟላ ሰነድ ሲቅርብ ሂሳቡ ይወራረዳል::

5) በፕሮግራሙ ላይ ለሚገኙና ሙሉ መስተንግዶና /የምግብና የመኝታ አገልግሎት/ ለሚዘጋጅላቸው አካላት በዐብይ ኮሚቴው ፀድቆ በሚቀርበው ዝርዝርና የቀን ብዛት መሠረት የኪስ ገንዘብ በቀን ብር100.00 /አንድ መቶ ብር/ የማይወራረድ ሂሳብ ይከፈላል::

6) የስልክ አገልግሎት ክፍያ በሚመለከት እንደ ስራ ሁኔታ በማየት በቴክኒክ ኮሚቴው ሲፈቅድ በቀን፣ በሰው ከብር 50-100 /ከሃምሳ እስከ አንድ መቶ ብር/ድረስ ከአስር ቀን የማይበልጥ ይከፈላል::

7) ለጉልበት ሥራ፣ ለቀን ሥራና ለመሳሰሉት ወጪዎች የሚከፈል ገንዘብ በቴክኒክ ኮሚቴ ሰብሳቢ ፀድቀው ሲቀርቡ ተፈፃሚ ይሆናሉ::

8) ከከተሞች ፎረም ሂሣብ ምርመራ ጋር የተያያዙ ክፍያዎች በሚኒስቴር መስርያቤቱ የአሰራር ሥርዓት አግባብ ባለው ኃላፊ ሲፈቀድ ይፈፀማል::

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Urban Development & Housing

ክፍል ሶስት

የፎረሙ የግዥ አሰራሮች

14. **የተመረጡ የግዥ ዘዴዎች፣**

ፕሮግራሙን ለማሳካት እንዲረዳ የሚያስፈልጉ የአገልግሎትና የዕቃ ግዥን ለማከናወን በመንግስት የግዥ መመሪያ ላይ በተመለከተው መሰረት የግልጽ ጨረታ፣ የውስን ጨረታ፣ የዋጋ ማቅረቢያ እና ከአንድ አቅራቢ የሚፈጸም የግዥ ዘዴዎችን በሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል። የግዥ ዘዴዎቹ በሥራ ላይ ሲውሉ በመንግስት የግዥ አዋጅና መመሪያ ላይ በተመለከተው የአፈጻጸም ሂደት ይሆናል።

15. **የግዥ አፈጻጸም ሂደት፣**

ከከተሞች ፎረም ጋር የተያያዙ ግዥዎችን ለመፈጸም ያስችል ዘንድ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መሟላት ይኖርባቸዋል፡-

1) ለፕሮግራሙ ማስፈጸሚያ የሚውል የአገልግሎትና የዕቃ ግዥ በሚመለከተው ኃላፊ የጸደቀ የዕቃ ግዢ መጠየቂያ ይቀርባል።

2) በሚቀርበው የዕቃና የአገልግሎት የግዥ ጥያቄ መሰረት እስከ ብር 5,000 ለሚሆኑ ግዥዎች በቀጥታ ከዕቃው አቅራቢ መግዛት ይቻላል።

3) ከብር 5,001 በላይ ለሆኑ የዕቃ ግዥዎች እስከ ብር 200,000 ድረስ፣ ለልዩ ልዩ የአገልግሎት ግዥዎች እስከ ብር 150,000 ድረስ፣ እንዲሁም ለግንባታ ሥራዎች እስከ ብር 500,000 ድረስ፣ ቢያንስ ሦስት የዋጋ ማቅረቢያዎችን ከተለያዩ ድርጅቶች እንዲቀርቡ እና እንዲወዳደሩ ይደረጋል።

4) በጎንደር ከተማ አስተዳደር በኩል በውክልና የሚፈፀሙ ግዥዎች በክልሉ የግዥ መመርያ መሰረት የሚፈፀም ይሆናል።

5) ግዥውን ለመፈጸም ተገቢውን ሰነድ በማዘጋጀት የሚገዛው አገልግሎት ወይም ዕቃ በመንግስትን የግዥ እና የፋይናንስ ደንብ መመሪያ መሰረት ይፈፀማል።

6) ለሚገዛው አገልግሎት ወይም ዕቃ በቀረበው የዋጋ ማቅረቢያ መሰረት ሰነዶቹን በመገምገም አሸናፊውን በመለየት በግዥ መመሪያው መሰረት እንደአስፈላጊነቱ የውሳኔ ሃሳብ ለግዥ አጽዳቂ ኮሚቴው ወይም ለቴክኒክ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይም ለአብይ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይም ለበላይ አመራሩ በማቅረብና በማጸደቅ ግዥው ከአሸናፊው ድርጅት እንዲፈጸም ይደረጋል፡፡

7) አሸናፊው ድርጅት እቃውን ወይም አገልግሎቱን እንዲያቀርብ እንደአስፈላጊነቱ ውል ተዘጋጅቶ ይፈፀማል፡፡ በተገባው ውል መሰረትም አገልግሎቱ መሰጠቱን ወይም ዕቃው መቅረቡን በሚመለከታቸው የኮሚቴ አባላት ወይም ኃላፊዎች ማረጋገጫ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡

8) የመንግስት መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት በተዘጋጁ ሞዴሎች ላይ የተገዛው ዕቃ ይመዘገባል፡፡

9) የተገዛውን ዕቃ ጠያቂው ክፍል በሞዴል ወጪ በማድረግ ይረከባል፤ ዕቃውም በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

10) የተገዛው ዕቃ ቋሚ ዕቃ ከሆነ የተረከበው አካል በጥንቃቄ በመያዝ ከፕሮግራሙ ፍጻሜ በኋላ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በሞዴል ተመላሽ ያደርጋል፡፡

11) የተገዛው ቋሚ ዕቃ ለአዘጋጁ የጎንደር ከተማ አስተዳደር እንዲሰጥ የተወሰነ ከሆነ በዝርዝሩ መሰረት የከተማ አስተዳደሩ የዕቃ ግምጃቤት ገቢ ማድረጊያ ሞዴል በማዘጋጀት ርክክቡ ይፈፀማል፡፡

12) የህትመት ፍላጎቶችን መጠንና ይዘት በሚመለከት የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት ለቴክኒክ ኮሚቴ አቅርቦ ካስወሰነ በኋላ በሚቀርብለት የፍላጎት ዝርዝር መሰረት የግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ግዥ ይፈጽማል፡፡

13) ለሽልማትና ለልዩ ልዩ ስጦታዎች የሚውሉ የአቅርቦት ፍላጎቶች መጠንና ይዘት በሚመለከት ለቴክኒክ ኮሚቴ የሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ወይም ኮሚቴዎች አቅርበው ካስወሰኑ በኋላ በሚቀርብለት የፍላጎት ዝርዝር መሰረት የግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ግዥ ይፈጽማል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Urban Development & Housing

ክፍል አራት

የፎረሙ የገቢ ምንጮች አሰባሰብ እና የገቢና ወጪ ዕቅድ አሰራሮች

16. የመመዝገቢያ ክፍያ፣

1) በ7ኛው የከተሞች ፎረም ኤግዚቢሽን ላይ ከ200 ከተሞች በላይ ይመዘገባሉ ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን፣ የምዝገባው ክፍያ

ሀ) ብር 2,500 /ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር/ ነባር የዩኤልጂዲፒ ድጋፍ ተጠቃሚ የሆኑት 19/ አስራ ዘጠኝ/ ከተሞች ለእያንዳንዳቸው ይሆናል። (ዝርዝራቸው በአባሪ አንድ ተያይዟል)

ለ) ብር 2,000 /ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር/ የዩኤልጂዲፒ ድጋፍ ተጠቃሚ የሆኑት 25 /ሃያ አምስት/ ከተሞች ለእያንዳንዳቸው ይሆናል። (ዝርዝራቸው በአባሪ ሁለት ተያይዟል)

ሐ) ብር1,500 /አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር/ ከዩኤልጂዲፒ ድጋፍ ተጠቃሚ ከሆኑት 44 ከተሞች ውጭ ላሉት ሁሉም የከተማ አስተዳደሮች ወይም በተሳታፊ ድርጅቱ ይሆናል።

2) የምዝገባ ጊዜውን በተመለከተ ተመዝጋቢ ከተሞች ክፍያቸውን እስከ መጋቢት 30 ቀን 2009 ዓ.ም. ድረስ ማጠናቀቅ የሚጠበቅባቸው ሲሆን፣ ከተሞቹ የሚፈለግባቸውን የምዝገባ ክፍያ በሚከተለው የባንክ ሂሣብ ቁጥር ገቢ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

3) ከመመዝገቢያና ከድንኳን ኪራይ የሚሰበሰበው ገቢ" በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ስም ለፎረሙ አገልግሎት በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ቁጥር" ይሆናል።

17. የኤግዚብሽን ቦታ /ድንኳን/ ኪራይ አከፋፈል፣

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ከሚያዝያ 22 - 28 ቀን 2009 ዓ.ም በጎንደር ከተማ አስተዳደር ይካሄዳል።

1) ለከተሞች ለሚያዘጋጁት ኤግዚቢሽን ለድንኳን ኪራይ እና ለመሳሰሉት በካሬ ሜትር ብር 250.00 /ሁለት መቶ ሃምሳ ብር/ ከተሞችና ተሳታፊ ድርጅቶች መክፈል ይኖርባቸዋል።

2) የድንኳኖቹም ስፋት ከ12 እስከ 600 ካሬ ሜትር ይሆናል።

3) ከተሞች በካሬ ሜትር የሚፈለግባቸውን ሂሣብ ኤግዚቢሽኑን በሚያሳዩባቸው ቀናት ልክ አስልተው እስከ መጋቢት 30 ቀን 2009 ዓ.ም. ድረስ ለፎረሙ በተከፈተው የባንክ ሂሣብ ቁጥር ገቢ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

18. ከእስፖንሰሮች የሚገኝ ገቢን በተመለከተ፣

ከዚህ ፕሮግራም ዓላማ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተቋማትና ድርጅቶች በማፈላለግ ለዝግጅቱ የሚሆን ገንዘብ ለሚያሰባስብ በተቋቋመው የስፖንሰር አፈላላጊ ኮሚቴ በኩል በሚቀርብ የቃል ኪዳን ፎርምና ዝርዝር መሰረት ገቢ ይደረጋል።

19. የገቢና ወጪ በጀት ግምት፣

ለፎረሙ በዓል አከባበር የሚሰበሰብ የገቢ ግምትና ከየንዑሳን ኮሚቴ በተሰበሰበ መረጃ መሰረት የወጪ ግምት በአባሪ ሶስት ተያይዟል። ይህ የገቢና ወጪ ግምት ወደስራ ሲገባ ሊለውጥ እንደሚችል ይገመታል።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Urban Development & Housing

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ አሰራሮች

20. የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት፣

1) የትራንስፖርት አቅርቦትን በተመለከተ ለፕሮግራሙ ዝግጅት የሚያስፈልጉ የትራንስፖርት ዓይነቶችን በዝርዝር በመለየት የሚሟሉበትን ሁኔታ በዝርዝር በማጥናት ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች እንዲሟላ ይደረጋል፡፡

2) የተዘጋጀውን ፕሮግራም ለማስፈጸም ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ለሚፈለገው አገልግሎት ለማቅረብ ካልተቻለ የተሽከርካሪ ፍላጎቶችን በዓይነትና በብዛት በመለየት ለቴክኒክ ኮሚቴው አቅርቦ በማስጸደቅ ከገበያ በኪራይ እንዲሟሉ ይደረጋል፡፡ የተሽከርካሪ አገልግሎት በኪራይ ሲሟሉ የመንግስትን የግዥ እና የፋይናንስ ደንብና መመሪያን በመከተል ይሆናል፡፡

21. የቢሮ ዝግጅት፣

በቴክኒክ ኮሚቴው ለፕሮግራሙ ሥራ ማከናወኛ እንዲረዳ የከተሞች ፎረም በሚካሄድበት ጎንደር ከተማ ለሚከፈተው ጊዜያዊ ቢሮ በተለያዩ የቋሚ ዕቃዎችና የአላቂ ዕቃዎች እንዲደረጅ ይደረጋል፡፡

1) ለጽ/ቤት ሥራ የሚያስፈልጉ የቋሚ ዕቃዎች በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚገኙ ከሆነና የመስሪያ ቤቱን መደበኛ ስራ በማያስተጓጉል መልኩ በውሰት በመውሰድ ወይም በዓሉ የሚካሄድበት ከተማ አስተዳደር ጋር በመነጋገር እንዲሟሉና በሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡

2) በግዥ መሟላት የሚገባቸው የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ከሆኑ የግዥ ሂደቱን ተከትሎ እንዲሟሉ ይደረጋል፡፡

22. ሂሣብ ማስመርመር፣

1) የከተሞች ፎረምን ሂሣብ እንቅስቃሴ የተሟላ ሪፖርት በማዘጋጀት ህጋዊ ፈቃድ ባለው የውጪ ኦዲተር እንዲመረመር ይደረጋል፣

2) የከተሞች ፎረምን አስመልክቶ የተደረገው የፋይናንስ እንቅስቃሴ ሂሳብ ፎረሙ ከተጠናቀቀ በኂላ በሶስት ወራት ውስጥ ይዘጋል፡፡

3) የከተሞች ፎረምን ሂሳብ አስመልክቶ ሂሳቡ ከተዘጋበት ቀጥሎ በሚገኙት ሶስት ወራት ውስጥ በኦዲተሮች ምርመራው ተጠናቆ ውጤቱ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሳቸው ይደረጋል፡፡

23. መመርያውን ስለ ማሻሻል

መመርያውን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በማናቸውም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል፡፡

24. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ፣

ይህ መመሪያ ለከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ሚኒ ካቢኔ ወይም ለሚኒስትሩ ቀርቦ ከፀደቀበት ከጥር 30 ቀን 2009 ዓ/ም ጀምሮ የ7ኛው የከተሞች ፎረም ሂሳብ ተመርምሮ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

ዶ/ር አምባቸው መኮንን

የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ሚኒስትር

አባሪ አንድ

ነባር የዩኤልጂዲፒ ድጋፍ ተጠቃሚ የሆኑ ከተማ አስተዳደሮች ዝርዝር

1. አዳማ ከተማ አስተዳደር
2. ቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር
3. ጅማ ከተማ አስተዳደር
4. ሻሸመኔ ከተማ አስተዳደር
5. ባህር ዳር ከተማ አስተዳደር
6. ኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር
7. ጎንደር ከተማ አስተዳደር
8. ደሴ ከተማ አስተዳደር
9. መቀሌ ከተማ አስተዳደር
10. አዲግራት ከተማ አስተዳደር
11. አክሱም ከተማ አስተዳደር
12. ሽሬ እንደስላሴ ከተማ አስተዳደር
13. ሃዋሳ ከተማ አስተዳደር
14. አርባምንጭ ከተማ አስተዳደር
15. ወላይታ ሶዶ ከተማ አስተዳደር
16. ዲላ ከተማ አስተዳደር
17. ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር
18. ሐረር ከተማ አስተዳደር
19. አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

አባሪ ሁለት

አዲስ የዩኤልጂዲፒ ድጋፍ ተጠቃሚ የሆኑ ከተማ አስተዳደሮች ዝርዝር

1. አሰላ ከተማ አስተዳደር
2. ቡራዩ ከተማ አስተዳደር
3. ሰበታ ከተማ አስተዳደር
4. አምቦ ከተማ አስተዳደር
5. ሮቤ ከተማ አስተዳደር
6. ባቱ ከተማ አስተዳደር
7. ነቀምት ከተማ አስተዳደር
8. ደብረ ብርሃን ከተማ አስተዳደር
9. ደብረ ታቦር ከተማ አስተዳደር
10. ወልደያ ከተማ አስተዳደር
11. ፍኖተሰላም ከተማ አስተዳደር
12. ሞጣ ከተማ አስተዳደር
13. ደብረማርቆስ ከተማ አስተዳደር
14. አላማጣ ከተማ አስተዳደር
15. ሁምራ ከተማ አስተዳደር
16. ውቅሮ ከተማ አስተዳደር
17. አድዋ ከተማ አስተዳደር
18. ሚዛን ከተማ አስተዳደር
19. ሆሳእና ከተማ አስተዳደር
20. አረካ ከተማ አስተዳደር
21. ቡታጅራ ከተማ አስተዳደር
22. ሰመራ ሎግያ ከተማ አስተዳደር
23. አሶሳ- ቤኒሻንጉል ከተማ አስተዳደር
24. ጋምቤላ ከተማ አስተዳደር
25. ጂግጂጋ-ሶማሌ ከተማ አስተዳደር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Urban Development & Housing

አባሪ ሦስት

1) ከመዋጮ የሚሰበሰብ ገቢ ግምት፣

ተቁ	የበጀት ምንጭ	የገንዘብ መጠን በብር
1	የኤግዚቢሽን ተሳትፎ ክፍያ (ከመመዝገቢያና ከድንኳን ኪራይ) 200 ከተሞች በአማካኝ 40 ካሬ ለ7 ቀን በቀን 250 ብር ከመመዝገቢያ 1500 ብር ጋር	14,300,000.00
2	የከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር ድርሻ መዋጮ	2,000,000.00
3	የጎንደር ከተማ አስተዳደር ድርሻ መዋጮ	5,000,000.00
4	ከስፖንሰሮች የሚገኝ ድጋፍ	2,500,000.00
	ድምር	23,800,000.00

2) የወጪ ግምት

ተ.ቁ.	የወጪ አይነት		የወጪ መጠን
1	ለኢግዝቢሽን ዝግጅት		
1.1	ድንኳን(በቀናት)		2,510,756.00
1.2	የኤሌክትሪክ እቃዎች		391,423.00
1.3	የድጋፍና ክትትል ስራ		242,000.00
1.4	ወንበሮችና ጠረጴዛዎች		435,600.00
1.5	ሌሎች አጋዥ መሳሪያዎች		96,800.00
1.6	የቦታ ዝግጅት		242,000.00
1.7	የአበልና ትራንስፖርት		145,200.00
1.8	ኤግዚብሽን ማስተባበሪ የሚባስ ኪራይ በቀን 3000 ለስድስት ቀን		18,000.00
1.9	መጠባበቂያ (10 ከመቶ)		408,178.00
	ድምር		**4,489,957.00**
2	የምርጥ ተሞክሮ ውድድር ዝግጅት		
2.1	ለትርጉም እና ኢዲቲንግ ስራዎች ክፍያ		70,000.00
2.2	ዲዛይን /ፖስተር/		30,000.00
2.3	ተሳታፊ ከተሞች የድጋፍና ማማከር ስራ		70,000.00
2.4	የዳኞች የውሎ አበል		45,000.00
2.5	የስጦታ ቴሌቪዥን ግዥ		155,000.00
2.6	የወርቅ ዋንጫ		15,000.00
2.7	ክርስቲያል ዋንጫ		24,000.00
2.8	ሜዳልያ		360,000.00
2.9	የቀጣይ ከተሞች ፎረም አዘጋጅ ከተማ ፋሬም		3,000.00
	ድምር		**772,000.00**

ተ.ቁ.	የወጪ አይነት		የወጪ መጠን
3	**የህፃናት የዜማ ውድድር**		
3.1	የተወዳዳሪዎች ሽልማት ወጪ		229,000.00
3.2	አሰልጣኝ		50,000.00
3.3	ለተሳታፊዎች የአበልና ትራንስፖርት		189,000.00
3.4	ለኮሚቴ አባላት አበል		40,800.0
3.5	አሰፈላጊ መሳሪያዎች ኪራይ እና ግዥ		50,000.00
3.6	የህጻናት ቲሸርትና ኮፍያ ወጪ		21,000.00
	ድምር		**579,800.00**
4	**ሴሚናርና የፓናል ውይይቶች**		
4.1	ጥናታዊ ጽሁፍ ለሚያቀርቡ ክፍያ		225,000.00
4.2	ለመስተንግዶ		300,000.00
4.3	ለጽህፈት መሳሪያዎችና ለወረቀት ማባዣ		40,000.00
	ድምር		**565,000.00**
5	**የ7ኛዉ የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የመዝናኛ ዝግጅቶች**		
5.1	ለሙዚቀኞች ክፍያ		60,000
5.2	ሙዚቃ ባንድ		150,000
5.3	ማርሽ ባንድ		38,500
5.4	የመድረክ ዝግጅት		165,000
5.5	የመድረክ ስቴጅ ማስዋቢያ የሚያስፈልጉ ግዥዎች		50,000.00
5.6	የመድረክ መሪዎች ጊዥ ክፊያ		100,000.00
5.7	ቢል ቦርድ ማስታወቂያ ድዛይንና ህትመት		100,000.00
5.8	ለሚዲያ ባለሙያዎች የዉሎ አበል ከተለያዩ የሚዲያ አካላት ተሳታፉ የሚሆኑ እና ከኢትዮጵያ ሬ/ቴ/ድርጅት የቀጥታ ስርጭት ባለሙያዎችን የሚያጠቃልል		240,000.00
5.9	ለሞባይል ካርድ		1,500.00
5.10	ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚሳተፉ የህዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች ዉሎ አበል		48,000.00
	ድምር		**953,000.00**
6	**የኮሚኒኬሽንና የሚዲያ ፕሮግራም**		
6.1	የቴሌቪዥን ሬድዮ ማስታወቂያዎች ዝግጅት		325,200.00
6.2	የቅድመ ምዝገባ ማስታወቂያ ለ10 ተከታታይ ቀናት እንዲተላለፍ ይደረጋል (በሰከንድ ለ2 ሚዲያ)		
6.3	ሁሉንም ሚዲያዎች በመጠቀም ስለ በዓሉ እንዲዘግቡ እና በቂ ሽፋን እንዲሰጡ ይደረጋል (የሻይ ቡና)		3,000.00
6.4	ለኢንቨቴሽን ጋርድ ፖስተር፣ ፎልደር		70,550.00
6.5	ለባጆች		97,900.00
6.6	ለመጽሔት ህትመት		60,500.00
6.7	ባነር		16,500.00

ተ.ቁ.	የወጪ አይነት		የወጪ መጠን
			10,000.00
6.8	ለብሮሸር		500,000.00
6.9	ፕረስ ኪት		62,093.00
6.10	የሬዲዮ ፕሮግራም		59,800.00
6.11	ለአርት ፋል የቴሌቪዥንና ሬድዮ ማስታወቂያዎች ዝግጅት ለፕሮዳክሽን		162,600.00
6.12	ለቴሌቭዥንና ሬዲዮ አየር ሰዓት ግዥ		31,046.00
6.13	ጋዜጣዊ መግለጫ		495,000.00
6.14	የቴሌቪዥን ቀጥታ ስርጭት የአየር ሰአት ግዥ		31,046.00
6.15	ፕሬስ ኮንፈረንስና የፕሬስ ሪሊዝ ዝግጅት		465,700
6.16	የቴሌቪዥን ሬድዮ የአየር ሰአት ክፍያ		**2,390,935.00**
	ድምር		
7	**የመስተንግዶ እና የጉዞ ወጪ**		838,459.18
7.1	የመስተንግዶ ወጪ		**880,100.00**
7.2	የጉዞ ወጪ አበልና ትራንስፖርት		**1,718,559.00**
	ድምር		
8	**ለህትመት ዝግጅት**		52,000.00
8.1	ፎቶ ኮፒ እና ጥረዛ		36,000.00
8.2	በራሪ ወረቀቶች		65,500.00
8.3	የባነር ዝግጅት		47,000.00
8.4	ፕሬስ ኪት		27,000.00
8.5	ዶከመንቴሽን እና አርትኦት		13,000.00
8.6	የመግቢያ ካርድ		560,000.00
8.7	የጥሪ ካርድ፣ብሮሸር ህትመት		367,900.00
8.8	ባጅ		270,000.00
8.9	የ7ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ሪፖርቶች፣ጋዜጦች እና መፅሄት ህትመት		1,500.00
8.10	ከአንጨት ተቀርፆ የሚሰራ ሰርተፍኬት		13,000.00
8.11	የታተመበት እስክርቢቶ		17,000.00
8.12	ሎጎ የታተመበት ባይንደር		13,000.00
8.13	ሎጎ የታተመበት ማስታወሻ ደብተር		13,500.00
8.14	የታተመበት ቲሸርትና ኮፍያ		**1,496,400.00**
	ድምር		
9.	**ልዩ ልዩ ወጪ**		25,000.00
9.1	ስቴሽነሪ ግዥ		3,000.00
9.2	ለመድረክ ማሸብረቂያ አበባ		640,000.00
9.3	በዝግጅት ቦታው ላይ ለሚሳተፉ የአበል ክፍያ(160ሰው በ400 ብር)		80,000.00
9.4	የመኪና ኪራይ		120,000.00
9.5	የነዳጅ ወጪ		35,000.00
9.6	የሞባይል ካረድ		**903,000.00**
	ድምር		
10	**የሂሳብ ምርመራ**		

ተ.ቁ.	የወጪ አይነት		የወጪ መጠን
10.1	ሂሳብ ለሚመረምሩ ኦዲተሮች ክፍያ		70,000.00
	ድምር		**70,000.00**
	ጠቅላላ ድምር		**13,938,651.00**
	መጠባበቂያ (10%)		**1,393,865.00**
	አጠቃላይ ድምር		**15,332,516.00**